## ሳምንታዊ ዜና ዘገባ

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ ጥር 9 ቀን 2001 ዓ.ም.

- አዲሱ የአሰራር ለዉጥ የሚለዉ የወያኔ የማባረር ዘመቻ ተጀመረ፣ በርካታ ዶክተሮች ምሁራን በምዘናዉ ዝቅተኛ ዉጤት በመስጠታቸዉ መዘናቸዉ ተጠቆመ፣
- ምንጠራዉ ወደ ወታደራዊ ተቋም ዉስጥ ይዘልቃል፣
- በድሬዳዋ ከተማ የተቀሰቀሰዉን ግጭት ያቀነባበረዉ የወያኔ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቡድን መሆኑ ተጋለጠ፣
- በአዲስ አበባም ተሞክሮ ከሸፈ፣
- በአዉቶቡስ ተራ የፈንጂ አደጋዉም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነዉ ተባለ፣
- አባ ገ/መድህን የተሰጠዉን ፀረ ህዘብ ግዳጅ ለመወጣት እየተሯሯጠ መሆኑ ታወቀ፣
- በአዲሰ አበባ ዉስጥ አንድ ወጣት በደህንነት ኃይሎች ተገደለ፣ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል።

ዝርዝሩን በሚቀጥለዉ ገጽ ያንብቡ <<<<>>>>

በቅርቡ ወያኔ አዲስ የአሰራር ለውጥ አድርጌያለሁ በሚል ከ20 ዓመታት በላይ ሲያገለግሉ የነበሩ መንግስታዊ መስሪያ ቤት ሰራተኞችን እያፈናቀለ መሆኑ ታወቀ:: ከስድስት ወር በፊት በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ አጠቃላይ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችን የወያኔ አባል ለማድረግ የሚቻለው እንዴት ነው በሚል ውስጥ ውስጡን ሲጠና አዲስ የአሰራር ለውጥ ወይም ቢ.ፒ.አር. በሚል መቀየስ እንዳለበት አቀነባብረው ሰርተው እንዳቀረቡት የገለፀው የደረሰን ዘገባ በአሁኑ ሰዓት በሁሉም መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ መሆን በመጀመሩ ሰራተኞች ለከፍተኛ ችግር ተዳርገው እንደሚገኙም አስረድቶዋል::

ለብዙ ዓመታት ህሙማንን ሲያክሙ የነበሩና በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታ ያላቸውን እውቀትና ልምድ ያካበቱ ዶክተሮችን ጨምሮ የህክምና ባለሙያዎች የወያኔ አባል ባለመሆናቸውና በወያኔ ላይ ጥላቻ ስላላቸው ብቻ በስውር አዲሱ አሰራር በሚል ምዘና ዝቅተኛ ውጤት እየሰጡዋቸው በሞራላቸው ላይ የማይሽር ጠባሳ እያሳረፉባቸው ከመሆኑም በላይ ባለሙያዎቹ በድርጊቱ ማዘናቸውን በየካቲት 12 እና በራስ ደስታ ሆስፒታል እየታየው ያለው ሀቅ ማስረጃ ነው ሲል ዘገባው ገልፆዋል::

እንደ ኮሚኒስት ስርዓት የሀገሪቱን የመንግስት ሰራተኞች በሙሉ በመሳሪያ ኃይል እያስፈራሩና በህዝብ ሀብትና ገንዘብ እየደለሉ የአንድ ፓርቲ አባል ለማድረግና በሀገሪቱ ውሰጥ ወያኔ ብቻ ዘለዓለም እየገዛ እንዲኖር ለማድረግ ከላይ ታች እየሮጠ ያለው መለስ ዜናዊ እና ቡድኑ አዲስ የአሰራር ለውጥ በሚል በርካታ ምሁራንንና ለብዙ ዓመታት ያገለገሉ ልምድ ያላቸውን አንጋፋ ሰራተኞች እያንሳፈፉ በምትካቸው ከመቀሌ ተመልምለው በመጡ ወጣት ካድሬዎች እየተተኩ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በየሆስፒታሉ ተግባራዊ የሆነው ይኸው አዲሱ የወያኔ ለውጥ ተብዬ ምንጠራ በፖለቲካ አቋዋማቸው ከወያኔ ጋር ያልወገኑና ያላኀበደዱትን ምዘና በሚል ዝቅተኛ ውጤት እየሰጡዋቸው ሞራላቸው እንዲላሽቅ እና በገዛ ፍቃዳቸው የስራ መልቀቂያ እንዲያስገቡ ለማድረግ ሲሆን፣ ነባር ሰራተኞች ሆነው አማራጭ የሌላቸው ደግሞ በቢሮ ውስጥ ያለምንም ስራ እንዲቀመጡ በመድረግ ላይ መሆናቸውን ዘገባው አብራርቶዋል::

ወያኔ በሀገሪቱ ህዝብ ላይ በተደጋጋሚ እያደረሰ ያለው በደል አልበቃ ብሎት አሁን ደግሞ ለብዙ ዓመታት በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩትን ሰራተኞች የወያኔ አባል አይደሉም ሊሆኑም ፍላጎት የላቸውም በሚል እየተመነጠሩ በምትካቸው ወጣት አፍለኛ ካድሬዎች ምንም ዓይነት እውቀትና ልምድ የሌላቸውን ከቀበሌ እስከ ሚኒስትር መስሪያ ቤት እየሰገሰጉዋቸው መሆኑንና ሀገሪቱዋንና ህዝቡዋን ወደ ማጡ እየከተቱዋት እንደሚገኝ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በቀበሌ ደረጃ 30 ወጣት ካድሬዎች የተመደቡ ሲሆን በሌሎች መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ በተለይ ደግሞ በየሆስፒታሉ ውስጥ አምስት አምስት ወጣት ካድሬዎች መመደባቸውን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ዋና ስራቸው የስለላ እና ሰራተኞቹን በስውር እንቅስቃሴያቸውን መቆጣጠር መሆኑንም ጨምሮ ገልፆዋል።

ሰሞኑን በተደረገው ምደባና አዲስ የስራ ድልድል የተባለው የወያኔ የማባረሪያ ስልት በርካታ ኢትዮጵያውያን ተንሳፍፈው ያለስራ የሰዓት ፊርማ ብቻ እንዲፈርሙ በመደረጉ ሁለት የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነባር የመንግስት ሰራተኞች በብስጭት እራሳቸውን እንዳጠፉ ዘገባው አስረድቶዋል።

ከዋና ስራ አስኪያጅ እስከ ተላላኪና ፅዳት ሰራተኛ ድረስ ያሉትን የመንግስት ሰራተኞች ለመሰለልና የያዙትን አቋዋም ለማረጋገጥ ብሎም ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት ለማድረግ የተመደቡት እነዚሁ ካድሬዎች በአብዛኛው ከመቀሌ ተመልምለው የመጡ ሲሆን በሌሎችም አካባቢዎች የተመለመሉትም ቢሆን የትግርኛ ቋዋንቋዋ ተናጋሪ መሆናቸውንና ለ15 ቀናት በአላጌ እና በዓለማያ እርሻ ኪሌጅ ውስጥ ኮርስ ተሰጥቶዋቸው የተመደቡ መሆኑ ታውቋዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባሉ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ከጥር 4 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ አዲሱ የስራ ለውጥ የተባለው የወያኔ ፀረ ህዝብ አደረጃጀት በስራ ላይ የዋለ ሲሆን በሌሎችም ክልሎች በተዋረድ ተግባራዊ መሆን እንደሚጀምር እና በርካታ ሰራተኞችም እንደሚንሳፈፉ፡ በተለይ በጦሩ ውስጥ በመከላከያ ሚኒስትር ፣በፌደራል ፖሊስ ፣በአዲስ አበባ ፖሊስ እና በማረሚያ ቤቶች ፖለስ አባሎች ላይ የሚደረገው የምንጠራ ስራ እጅግ ሰፊ እንደሚሆን ዘገባው ምንጮቹን ዋቢ አድርጎ ገልፆዋል።

በሲቪል መንግስታዊ ተቋዋሞቹ የተጀመረው ይኸው አዲሱ ምደባ ወደ ወታደራዊ ተቋዋሞቹ ሲገባ በማባረር ፣በጡረታ ማስወገድ፣ ያለስራ ማስቀመጥ እና ከቦታ ወደ ቦታ የማዛወር ዘመቻ እንዳለበትና በዚህ ዘመቻ ካለፈው ግምገማ ወቅት ተርፈው የመጡ የነበሩ ነባር የወታደራዊ ተቋዋሙ ሰራተኞችና መኮንኖች ሊመነጠሩ እንደሚችሉ ዘገባው ተገልፆዋል።

ወያኔ በውስጡ ባለው ውስጣዊ ችግር እና በደረሰበት የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ኪሳራ ሊያገግም ያልቻለ ሲሆን፣ ሰሞኑን በድሬዳዋና በአዲስ አበባ ከተሞች ውስጥ በሀይማኖት ሰበብ በህዝቡ መሀከል ክፍተት እንዲፈጠር እና ግጭት እንዲቀሰቀስ ሙከራ ሲያደርግ እንደነበረና አሁንም እንደቀጠለበት ለደህንነት ቢሮ ቅርበት ያላቸው ምንጮች አጋልጠዋል።

ታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓ. ም. የገና በዓል በሚከበርበት ዕለት የክርስትና እምነት ተከታዮች በድሬዳዋ ከተማ እየተዘዋወሩ በመዝሙር ሲያከብሩ በወያኔ ብሔራዊ ደህንነትና መረጃ ክፍል በተዘጋጁ ወጣቶች አማካኝነት ግጭት እንዲፈጠር ከፍተኛ ሴራ ተጠንስሶ ግጭቱ የተከሰተ መሆኑን የገለፁት የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ የሁለት ሰዎች ሞትና ፖሊሶቹን ጨምሮ ከ80 ሰዎች በላይ ቀላልና ከባድ የመቁሰል አደጋ እንዲደርስ ማድረጋቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ሰሞኑን በድሬዳዋ ከተማ ግጭቱ እንዲቀሰቀስ በወያኔ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቡድን ከፍተኛ ሴራ የተሰራ ቢሆንም በህዝቡ ከፍተኛ አርቆ አስተዋይነት እና በእድሜ ባለፀጋ አባቶች እንዲሁም በአካባቢው ተወላጆች ባደረጉት ጥረት ብዙ ጉዳት ሳይደርስ ሊከሽፍ እንደቻለ የገለፁት ምንጮች በአዲስ አበባ ከተማም ውስጥ በመርካቶ አካባቢ ህዝብን የሚያጋጭ ፅሁፍ ያለበት በራሪ ወረቀቶች እየበተኑ ለማጋጨት ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም በእድሜ ባለፀጋ የሀይማኖት አባቶች ጥረት ወያኔዎች ያሰቡት ሳይሳካ እንደቀረ ምንጮቹ ገልፀዋል።

በወያኔ የብሔራዊ ደህንነትና መረጃ ቡድን የተቀነባበረው ይኸው አደገኛ ዝግጅት ተግባራዊ ለማድረግ የተላኩት ግለሰቦች የተሰጣቸውን ግዳጅ በአግባቡ ሳይወጡ አስቀድሞ በህዝቡ ዘንድ በመታወቁ የታሰበው ሳይሳካ ሲቀር ተልዕኮዋቸውን ያልተወጡትን የወያኔ የደህንነት አባሎች መልሰው ህዝብን ከህዝብ ጋር ልታጋጩ ነበር በሚል ሰበብ አስረው መግለጫ እንደሰጡባቸው ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ገለፃ ለመረዳት ተችሎዋል።

አብዮት ልጆቹዋን ትበላለች እያሉ የደርግ ባለስልጣናት የገዛ ካድሬዎቻቸውን እየገደሉ እንደነበሩት ሁሉ ዛሬም የወያኔ ባለስልጣናት የራሳቸውን ነባር ካድሬዎች ሳይቀር እየቀረጠፉ እዚህ ደረጃ ላይ የደረሱ ቢሆንም አሁንም ሰሞኑን የተሰጣችሁን ግዳጅ በአግባቡ አልተወጣችሁም በሚል ምክንያት የደህንነት አባሎቹን እስኮ መስመር በሚገኘው ምስጢራዊ እስር ቤት እንዳሰሩዋቸው ምንጮቹ ገልፀው በቀጣይም እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል ሲሉም ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል።

በህዝብ መሀከል ሰላም፤ ፍቅርና አንድነት ሲኖር እንቅልፍ የሚነሳው የወያኔ ቡድን በድሬዳዋና በአዲስ አበባ ከተማ መርካቶ አካባቢ የሞከረው ሰንካላ ሙከራ አልሳካ ሲለው በሌላ ዘዴ ተጠቅሞ ወደ ክፍለ ሀገር አውቶቡስ ተራ ህዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ ላይ ፈንጂ አጥምዶ አደጋ ለማድረስ በድጋሚ ሙከራ ቢያድርግም ይሕም ሳይሳካ በመቅረቱ ግዳጁን እንዲወጣ የተሰጠው ግለሰብ በአግባቡ ጊዜውን ባለመጠበቁ ግዳጁ ከሚፈፀምበት ቦታ ሳይደርስ መንገድ ላይ ፈንድቶ እራሱን ጨምሮ 32 ሰዎችን ሊያቆስል እንደቻለ ምንጮቹ አብራርተዋል።

ሐሙስ ጥር 7 ቀን 2001 ዓ. ም. ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ላይ ክፍለ ሀገር አውቶቡስ ተራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሲደርስ ግዳጅ የተሰጠው የደህንነት አባል በቦርሳ ታሽጎ የተሰጠውን ፈንጂ ከንጋቱ 12 ሰዓት ከ30 ደቂቃ ላይ እግቢ ደርሶ ህዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ላይ አስቀምጦ መሰወር እንደነበር ያጋለጡት ምንጮቹ ግለሰቡ ሰዓቱን ጠብቆ ባለመገኘቱና 30 ደቂቃ ዘግይቶ በመድረሱ በእጁ እንደያዘው ሊፈነዳ እንደቻለና በራሱ ላይ አደጋው እንደደረሰ ለማወቅ ተችሎዋል::

ለሽፋንነት ይረዱኛል በሚል ወንድሙን እና ባለቤቱን አስከትሎ የነበረ በመሆኑ እነሱም ላይ መጠነኛ የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸውም ምንጮቹ ጨምረው የገለፁ ሲሆን ሁሉም ቁስለኞች ወደ ራስ ደስታ ሆስፒታል ተወስደው ህክምና ተደርጎላቸው የተመለሱ ሲሆን የደህንነት አባሉ በእጆቹና በእግሮቹ ላይ ባሉ አጥንቶች ላይ በደረሰው ከፍተኛ ቁስለት ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል እንደተወሰደና በዚያው ተኝቶ በፖሊስ እየተጠበቀ እንደሚገኝ ምንጮቹ አስረድተዋል::

ከብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት ስልጠና ተሰጥቶት ግዳጅ ተቀብሎ ሳይሳካለት የቀረው ግለሰብ እራሱን ጨምሮ 32 ሰዎች ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው ቢሆንም ዋናው ዓላማ የነበረው በዚህ የክፍለ ሀገር አውቶቡስ ተራ ግቢ ውስጥ የመላ ሀገሪቱ ተጉዋዦች የሚገኙበት በመሆኑ ሁሉንም ብሔር ተወላጆች ለመቀስቀስ እንዲያመች አደጋ ለመጣል እንደነበረ ምንጮቹ ገልፀዋል::

በወያኔ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቡድን በኩል እንዲህ ያለ አስነዋሪና ህዝብ ጨራሽ ተልዕኮ እንዲፈፀም ለማድረግ ያሰበው በህዝቡ ዘንድ የመወያያ ርዕስ ሆኖ እንዲሰነብትና የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር እንዲሁም በዚህ ሰበብ የሚፈልጋቸውን ሰዎች ለማፈስ እና ለእስር ለመዳረግ መሆኑንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

በወለጋ ክፍለ ሀገር በሳሲጋ አውራጃ ውስጥ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቡድን ያሰማራው የታጠቀ ኃይል በአካባቢው በሚኖሩ ህዝብ ላይ በድንገት ዘልቆ ገብቶ ከ80 ሰዎች በላይ ገድሎ ከ300 በላይ አቁስሎ የተቀሩትም ቀዬአቸውን ጥለው እንዲሰደዱ አድርጎ እንደነበር መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን አሁንም ስጋት ያለባቸው አቅጣጫዎች ላይ አደጋ እንዲከሰት እየተውጠነጠነ መሆኑንም ምንጮቹ አብራርተዋል::

ሰሞኑንም የጥምቀት በዓል ካለፈ በሁዋላ ባሉ ሳምንታት አንደኛው እሁድ ቀን በመስቀል አደባባይ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ዕቅድ መውጣቱን የዘገብን ሲሆን በአሁኑ ሰዓትም ዝግጅቱ ተጠናቅቆ ቀን መቁረጥ ብቻ እንደቀረ የቤተክህነት ምንጮች አጋልጠዋል::

ተሳስቦና ተፋቅሮ የኖረውን ህዝብ ለማለያየት በወያኔ ቡድን የተጀመረው አልሳካ ሲላቸው በየእምነቱ ስፍራ ሁሉ ጣልቃ እየገቡ ብጥብጥና ሁከት እንዲነሳ እያደረጉ

ከመሆኑም በተጨማሪ ሰሞኑንም አባ/መድህን ህዝበ ክርስቲያኑን በየደብሩ ላሉት አለቆች ትዕዛዝ ሰጥቶ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ዝግጅቱን ያጠናቀቀ ሲሆን የዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ዋነኛ ድብቅ አጀንዳ የክርስትና እምነት ተከታዮችን ከተቀረው ወገኑ ጋር ለማጋጨትና ለማበጣበጥ ብሎም በሀገሪቱ ሰላም እንዳይኖር ለማድረግ መሆኑን ጠቁመው እግረመንገዳቸውን በአሜሪካ የሚገኘውን በአቡነ መርቀርዮስ የሚመራውን ሲኖዶስ ለማውገዝ መሆኑንም ምንጮቹ አብራርተዋል።

ለዚህም ይረዳ ዘንድ ኮሚቴ ተዋቅሮ ያለ ሲሆን አንዳንድ ጳጳሳት ድርጊቱን በማውገዝ ይህ የፖለቲኞች እንጂ የእኛ የእምነት አባቶች ተግባር አይደለም እያሉ ተቃውሞ እያሰሙ ቢሆንም ሰሚ አጥተው እንደቀሩና ውስጥ ውስጡን ግን ኩርፊያው የጠነከረ መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ያስረዳል።

የወያኔ ቡድን በህዝቡ ላይ በሰራው ወንጀል ብዛት እየደነበረ የገዛ ጥላውን እየፈራ ያለምንም ወንጀል በተለይ ወጣቶችን እያፈሰና እያሰረ ከመሆኑም በተጨማሪ በቀዝቃዛ ውሀ በሞላ በርሜል ውስጥ እየነከረ እንደሚደበድባቸው ከተለያዩ ስፍራዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ገለፁ።

በአዲስ አበባ ፣በጅማ፣ በድሬዳዋ፣ በባህር ዳር፣ በናዝሬት እና በሌሎችም ከተሞች ውስጥ ያሉ የደህንነት አባሎችና የፌዴራል ፖሊሶች በየአካባቢው ባሉ ወጣቶች ላይ የእስራት እና የድብደባ እርምጃ እየወሰዱባቸው ወጣቶቹ እየተማረሩ ቢሆንም ሰሞኑን ደግሞ ድብደባው ወደ ነጻ ዕርምጃ ተሸጋግሩዋል።

ማክሰኞ ጥር 5 ቀን 2001 ዓ. ም. ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ በሰላም ወደ ቤቱ ሲጉዋዝ የነበረ ወጣትን ሁለት የደህንነት አባሎች በግዳጅ ለመውሰድ ቢጠይቁትም የፍርድ ቤት መጥሪያ ወረቀት ሳታሳዩኝ የትም አልሔድም በማለት ሲከራከራቸው በታጠቁት ሽጉጥ ተኩሰው ደረቱ ላይ ደጋግመው በመምታት እንደገደሉትና በወቅቱ አጠገቡ የነበረውንም ወጣት እግሩን በመምታት እንዳቆሰሉት ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድተዋል።

ሁለቱ የደህንነት አባሎች በአዲስ አበባ ከተማ አብነት አካባቢ አንደኛውን በመግደል ሌላኛውን በማቁሰል የተሰወሩ ቢሆንም ህዝቡ ቁስለኛውን አንስቶ ወደ ሆስፒታል ለመውሰድ በመረባረብ ላይ በነበረበት ወቅት የፌዴራል ፖሊሶች በአካባቢው ላይ ደርሰው እንዳባረሩዋቸውና የቆሰለው ወጣትም ሳይነሳ ብዙ ደም እንዲፈሰው ያደረጉ ቢሆንም ህዝቡ በድፍረት እኛንም ግደሉን እያለ እየጮኸ እንዳነሱትና እንደወሰዱት ዘገባው አብራርቶዋል። .

የወያኔ  ባለስልጣናት የሀገሪቱን ሀብት በራሳቸው እና በቤተሰቦቻቸው ስም መዝብረው ህዝቡን ለድህነት  ዳርገውት ባለበት በዚህ ወቅት ላይ በራሳቸው ጥረት ጥረው ግረው ሀብት ያፈሩትን ኢትዮጵያዊ ባለሀብቶች እያስፈራሩና እያስጨነቁ እራሳቸውን እንዲያጠፉ እያደረጉ መሆኑን የሰሞኑ መነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ መሰንበቱ ታወቀ።

በሀገሪቱ  ውስጥ አሉ ከተባሉት ባለሀብቶች መካከል አንዱ ሰሞኑን ድንገት የሞቱት አቶ ዱጉማ ሁንዴ ዲ.ኤች.ገዳ በሚል ግዙፍ የተለያየ ስራ ላይ የተሰማሩ ፋብሪካዎች ባለቤት በድንገት የሞቱበት ዋነኛ ምክንያት የወያኔ ባለስልጣናት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ  በማስፈራራት በውጭ ሀገር ያስቀመጥከውን የውጭ ሀገር ብር /ዶላር/  አምጣ እያሉ እንደነበረ ለባለሀብቱ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀው ባለሀብቱ ሰርቼ እንጂ ሰርቄ አይደለም ያጠራቀምኩት የሚል ምላሽ በመስጠታቸው የወያኔ ባለስልጣናትን እጅግ እንዳስኮረፈና ዘመቻውም ከዚህ የጀመረ መሆኑን ቅርበት ያላቸው ወገኖች አስረድተዋል።

አቶ ዱጉማ ሁንዴ ይህንን ድፍረት ቃል የተቀላቀለበት ንግግር ያደረገው ከጀርባው ምን ቢኖር ነው በሚል የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ደህንነቶችን አሰማርተው በአይነ ቁራኛ እየጠበቁና እያዋከቡ እንደሰነበቱ የገለፁት ቅርበት ያላቸው ወገኖች ከመሞታቸው አስቀድሞ በነበሩት ቀናቶች ውስጥ ብቻቸውን ሆነው መዋልን ይመርጡ እንደነበረም ጨምረው ገልፀዋል።